# የ5ኛ ክፍል 1ኛ ማርክ መስጫ ክፍለ ጊዜ የወላጆች መመሪያ

በ1ኛ ማርክ መስጫ ወቅት፣ የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች ከዚህ በታች በተገለፁት ፅንሰሃሳቦች እና ክሂሎቶች ትምህርት ይቀበላሉ።

*እባክዎ ልብ ይበሉ፦ በሠማያዊ ቀለም/ከለር የሚታዩት ክህሎቶች እና ጽንሠሃሳቦች ትምህርት ተሰጥቷል፣ ነገር ግን በሪፖርት ካርድ ላይ ማርክ አልተጻፈም።*

## የሂሳብ ትምህርት

### መለካት እና የተመዘገበ መረጃ

- በሙሉ ቁጥር የጎን ርዝመት መለኪያ በአሃዱ ኪዩብስ በማጨቅ የራይት ሬክታንጉላር ፕሪዝም ይዞታ መፈለግ፣ እና ይዘቱ የጠርዝ ርዝመትን በእኩዮሽ በመሠረት ስፋት ቁመት በማባዛት ከሚገኘዉ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ማሳየት።
- በገሀዱ ዓለም እና የሂሳብ ፕሮብሌምን የመፍታት አዉድ ዉስጥ V = l × w × h and V = b × h ቀመሮችን ለአራት ማእዘናዊ ፕሪዝሞች ትግበራ በመጠቀም ባለ 90 ዲግሪ አራት ማእዘን ባለ ሙሉ ቁጥር ጠርዝ ርዝመት ጋር መጠኑን አግኝ/ኚ።
- ይህን ቴክኒክ የተጨባጭ ኣለም ፕሮብሌሞችን ለመፍታት ተግባራዊ ለማድረግ፣ ሁለት ያልተደራረቡ ባለኣራት ማእዘን ፕሪዝሞችን የያዙ ድፍን ነገሮችን መጠን የማይደራረቡትን ክፍሎች መጠኖች በመደመር ማግኘት።

### ቁጥሮችና ግብረቶች በኣስሮሽ ቤት

- በርካታ ድጂት ያለው ቁጥር ላይ በአንድ ቦታ ላይ ያለ ዲጅት የሚወክለው በስተቀኙ ያለው ዲጅት ከሚወክለው 10 ጊዜ በይበልጥ እና ከበስተግራ ካለው ድጅት 10 ጊዜ ያነሰ እንደሚሆን ተገንዘብ/ቢ።
- ዴሲማሎችን ወደ ሺህዎች ማንበብ፣ መፃፍ፣ እና ማወዳደር።
- ባለ-ብዙ-ኣሃዝ ሙሉ ቁጥሮች በመደበኛ የሂሳብ ኣሰራር/algorithm በቅልጥፍና ማባዛት።
- በነጥብ የሚከፈሉ ቁጥሮችን/ዴሲማሎችን በመቶዎች ደምር(ሪ)፣ ቀንስ(ሺ)፣ አባዛ(ዢ)፣ እና አካፍል(ይ)፤ ስልቱን ወደ ጽሑፍ ዘይቤ በማገናኘት ምክንያቱን አስረዳ(ጂ)።

### ስሌቶች እና የአልጀብራ አስተሳሰብ

- በቁጥር ስሌቶችን የሚመዘግቡ ቀላል መግለጫዎች መፃፍ፣ እናም የቁጥር መግለጫዎች ሳይገመገሙ መተርጎም።

## ምንባብ

### የማንበብ ግንዛቤ፦ ስነ ፅሁፍ

- ጽሁፉ በተለይ ምን ላይ እንደሚያተኩር ስታብራራ(ሪ) እና ከእውነታው በመነሣት ድምዳሜ ላይ ስትደርስ(ሺ) ከጽሑፍ ላይ በትክክል ጥቀስ(ሺ)።
- በጽሑፍ ላይ ካለው ዝርዝር በታሪኩ ላይ ያለው ገጸባህርይ ለአስቸጋሪ/ተፈታታኝ ሁኔታዎች እንዴት ምላሽ እንደሚሰጥ ጭምር ዋናውን ጭብጥ ወስን/ኚ።
- በጽሑፍ ውስጥ የተወሰኑ ዝርዝሮችን በማንሳት፣ በአንድ ታሪክ ውስጥ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ገጸባህርያትን፣ መቼት፣ ወይም ሁነቶችን ያወዳድሩ እና ያነጻጽሩ።
- ተከታታይ ምዕራፎች እርስ በርሳቸው ተገጣጥመው የኣንድ ልዩ ታሪክ ኣጠቃላይ መዋቅር እንዴት እንደሚሰጡ ማብራራት።
- የተራኪ ወይም የተናጋሪ አመለካከት በሁኔታዎች አገላለጽ ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ግለጽ/ጪ።
- በ5ኛ ክፍል ደረጃ በሚገባ ውስብስብ የሆነ ስነ-ጽሑፍን ኣንብቦ መገንዘብ።

### ምንባብ የመረዳት (የማወቅ) ችሎታ፦ መረጃዊ

- ፅሁፉ በግልፅ የሚለውን ሲያብራሩ እና ከፅሁፉ መረጃ ሲወስዱ ከፅሁፉ በትክክል መጥቀስ።
- ከተከታታይ የፅሁፍ መዋቅር ጋር በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ፅሁፎች የቀረቡ ኣጠቃላይ የክውነቶች፣ የኣስተያየቶች፣ ወይም የመረጃዎች መዋቅር ማወዳደርና ማነፃፀር።
- በሚወክሉት ኣስተያየት ውስጥ ኣስፈላጊ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን እያመላከቱ፣የተመሳሳይ ክውነት ወይም ርእስ በርካታ ትረካዎችን መተንተን።
- ለ5ኛ ክፍል በኣግባቡ ውስብስብ የሆነ መረጂያዊ ፅሁፍ ማንበብና መገንዘብ።

### ቋንቋ፦ የቃላት ዝርዝር ግኝት እና ኣጠቃቀም

- ስለ 5ኛ ክፍል ርእሶችና ፅሁፎች፣ በሌሎች ኣስተሳሰቦች ላይ እየገነቡ እና የየራሳቸውን በግልፅ እየገለፁ በትብብሮሽ ውይይቶች ስብስብ በውጤታማነት መሳተፍ።
- ድምፅ ከፍ ተደርጎ የተነበበ ፅሁፍን ወይም በተለያዩ ሚድያና፣ በሚታይ፣ የብዛት እና የቃልን የሚያካትቱ ቅርፀቶች የቀረበ መረጃን ማጠቃለል።

## ጽሑፍ

### ትረካ

- እውነተኛ ወይም ሃሳብ የወለዳቸው ተሞክሮዎችን ወይም ክውነቶችን ለማዳበር በውጤታማ ቴክኒክ፣ ገላጭ ዝርዝሮች፣ እና በጠሩ የክዉነት ቅደም-ተከተሎች በመጠቀም ትረካ መጻፍ።
- ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተራኪ እና/ወይም ገጸ-ባህሪያትን ማስተዋወቅ፤ በተፈጥሮ የሚገለፀውን የክስተት ቅደም ተከተል ማደራጀት፤ ታሪኮችን እንደ ውይይት፣ መግለጫዎች፣ እና በመንቀሳቀስ/በዝግታ አቀራረብ የመሳሰሉ ትረካዊ ቴክኒኮችን መጠቀም ፣እና ከተረኩባቸው ልምዶች ወይም ክስተቶች የተገኘውን መደምደሚያ ማቅረብ።

### መረጃ የሚሰጥ/ትምህርታዊ/ገላጭ

- ኣንድን ርእስ ለማገናዘብና እስተያየቶችንና መረጃዎችን በግልፅ ለማስተላለፍ መረጃያዊ/ገላጭ ፅሁፎች መፃፍ።
- ኣንድን ርእስ በግልፅ ማስተዋወቅ፤ ኣጠቃላይ ትዝብትና ትኩረት መስጠት፤ ርእሱን ከሃቆች፣ ፍቺዎች፣ ጭብጥ ዝርዝሮች፣ ጥቅሶች፣ እና ከቡድን-ጋር-የተዛመዱ መረጃዎች ጋር በሎጂክ ማዳበር፤ ማጠቃለያ ኣረፍተሃሳብ ወይም ክፍል መስጠት፤ ቅርፀቶች (ለምሳሌ፣ ኣርእስቶች)፣ ስእሎች እና ባለበርካታ-ሚድያን ግንዛቤን ለማገዝ ጠቃሚ ከሆነ፣ ማካተት።

### ኣስተያየት

- በርእሶች ወይም በፅሁፎች ላይ በምክንያቶችና በመረጃዎች እየደገፉ የአመለካከት አጫጭር ድርሰቶችን አስተያየት ፃፍ/ፊ።
- አንድን ርእስ ወይም ጽሑፍ በግልጽ አስተዋውቅ/ቂ፣ ሃሳብን በመግለጽ፣ በእውነት፣ ተጨባጭ ነገር ላይ የተመሰረተ ዝርዝር እና አሳማኝ/ተቀባይነት ያለው አመክንዮ አቅርብ/ቢ፣ የመደምደሚያ ዓረፍተ ነገር ወይም ክፍል ማቅረብ፣ እና የጸሐፊው(ዋ)ን ዓላማ ምክንያታዊ በሆነ አገላለጽ በመደገፍ ሃሳቦች አንድ ላይ በቡድን የተቀናጁበትን ድርጅታዊ መዋቅር መፍጠር።

### ሂደት፣ ውጤት፣ ጥናት/ምርምር

- እድገቱና ኣደረጃጀቱ ለተግባር፣ ኣላማ፣ እና ለኣድማጭ ተገቢ የሆነ ጥራት ያለውና ስሙሙ ፅሁፍ ማቅረብ።
- ከእኩዮችና ከኣዋቂዎች የተወሰነ ኣመራርና ድጋፍ ጋር፣ ፅሁፍን ለማፍለቅና ለማተም እንዲሁም ከሌሎች ጋር ለመገናኘትና ለመተባበር በቴክኖሎጂ፣ ኢንተርኔትን ጨምሮ፣ መጠቀም።
- ለተለያዩ ሥርዓት-ተኮር ተግባራት፣ ኣላማዎች እና ታዳሚዎች ዳጋግሞ ለረጅም የጊዜ መቃኖች (የምርምር፣ ማሰላሰያ፣ እና የክለሳ ጊዜ) እና ኣጠር ላሉ የጊዜ መቃኖች (ለኣንድ-ኣፍታ ወይም ለኣንድ ወይም ሁለት ቀን) መፃፍ።

### የቋንቋ አጠቃቀም

- ዋነኛ ኣስተሳሰቦችን ወይም ዘውጎችን ለመደገፍ በኣንድ ርእስ ወይም ፅሁፍ ዘገባ ማቅረብ ወይም ኣስተሳሰቦችን በሎጂክ ቅደም-ተከተል በመስጠት እና በተገቢ ሃቆችና ኣስፈላጊ፣ ገላጭ ዝርዝሮች በመጠቀም፣ ኣንድ ሃሳብ ማቅረብ፤ በሚገባ ፍጥነት በግልጽ መናገር።
- የዋነኛ ኣስተሳሰቦች ወይም ዘውጎች እድገትን ለማበልፀግና መግለጫ ሲሰጥ ተገቢ ሲሆን ባለ-በርካታ-ሚድያ (ለምሳሌ፣ ግራፊኮች፣ ድምፅ) እና የሚታዩ ትርእይቶች በማካተት።
- በመፃፍና በንግግር የመደበኛ እንግሊዘኛ ስዋስውና ኣጠቃቀም ደንቦች በቂ ችሎታ ማሳየት።

## ሳይንስ

### ፊዚካል ሳይንስ

- ቁሳቁሶችን በጠባያቸው በመመስረት ለመለየት ትዝብቶችንና መለካቶችን ማድረግ።
- በሙቀት፣ በቅዝቃዜ፣ ወይም ቁሶችን በማደባለቅ፣ የሚያስከትሉ ለውጦች ቢኖሩም መጠናቸውን በመለካት እና ግራፍ/ሠንጠረዥ በመሥራት የቁስ አካል ክብደት የተጠበቀ መሆኑን ማስረጃ አቅርብ/ቢ።
- ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ነገሮች ቢደባለቁ ኣዲስ ነገር ይፈጥሩ እንደሆነ ለመወሰን ምርመራ ማካሄድ።

### ምህንድስና ንድፍ እና ሂደት

- ለቋቁሶች፣ ጊዜ፣ ወይም ዋጋ ስኬትና ማእቀቦች የተለዩ መስፈርቶችን የሚያካትት ኣንድን ችግር ወይም ፍላጎት የሚያንፀባርቅ ቀላል የንድፍ ፕሮብሌም መበየን።

- ለአንድ ፕሮብሌም በርካታ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ፣ እያንዳንዳቸው የፕሮብሌሙን መስፈርቶችና ግዴታዎች እንዴት እድርጎ ኣሳምሮ እንደሚያሟላ መሰረት በማድረግ፣ ማፍለቅና ማወዳደር።
- ተለዋጮች ቁጥጥር ስር የሆኑባቸውና የመውደቂያ ነጥቦች መሻሻል የሚችሉ የሞዴል ወይም የፕሮቶታይፕ ገፅታዎችን ለመለየት የሚታሰቡበት ፍትሃዊ ፈተናዎች ፕላን ማድረግና ማከናወን።

## ማህበራዊ ጥናቶች

### ኤኮኖሚክስ

- በአሜሪካ የቅኝ ግዢ ወቅት ከሸቀጦችና ከኣገልግሎቶች የኤኮኖሚ ፍላጎቶች ኣንፃር የሃብቶች/መገልገያዎች እጠረት በመኖሩ ሰዎች ምርጫዎች ማድረግ እንደነበረባቸው ማብራራት።
- በኮሎንያል አሜሪካ የኤኮኖሚ አቅጣጫ/ሲስተም እንዴት እንደሆነ መግለጽ።

### ታሪክ

- በሜሪላንድ ውስጥ በቡድኖችና በባህሎች መካከል የመስተጋብር ውጤቶችን ማገናዘብ።
- በ1880ዎቹ ዓመታት በሜሪላንድ የተካሄዱ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ እና ማህበራዊ ለውጦችን አስረድ(ጂ)።
- የአሜሪካ በቅኝ ኣገዛዝ ወቅት እድገትንና መዳበርን መተንተን።
- የኣሜሪካንን አብዮት ምክንያቶችና ውጤቶችን መተንተን።

## የመረጃ/ኢንፎርሜሽን ማንበብ እና መጻፍ/መሰረታዊ ትምህርት

- የተፈላጊ መረጃን ግኙቶች/መደምደሚያዎች ለማጋራት ለማዘጋጀት በተለያዩ ቅርፀቶች መጠቀም።
- የምንጭ ዝርዝር ለመፍጠር ተገቢ እና ተቀባይነት ባገኘ የመጥቀሻ ዘይቤ መጠቀም።

## ስነጥበብ

### ስነጥበብን መፍጠርና መገናኘት

- በስነጥበብና በሌሎች መስኮች አስተያየቶችን ለመተርጎምና ለመግለፅ የሚታዩ የስነጥበብ ሂደቶች መምረጥና ኣገልግሎት ላይ ማዋል።
- የሰነጥበብ ንጥረነገሮችን እና የንድፍ መርሆዎችን ማደራጀት፡- ቅርፀት፣ ድግግሞሽ፣ ንፅፅር፣ ምት፣ እንቅስቃሴ፣ ሚዛን፣ ኣንድነት፣ እና ኣፅንኦት ለተዛቡት ወይም ላዩት ምላሽ ስነጥበብን ለመፍጠር።

### ስነጥበብ አቀራረብና ዝንባሌ/ምላሽ

- የሰዎች፣ እንስሶች፣ እና የነገሮች ኣካላዊ ጠባዮች በስነጥበብ ንጥረ ነገሮች እንዴት እንደሚወከሉ መተንተን።
- በዘውግ፣ ይዘት፣ ፎርም፣ እና በዘይቤ ተመሳሳይነቶችንና ልዩነቶችን ለመወሰን የተለያዩ የስነጥበብ ስራዎችን መተንተን።

## ሙዚቃ

### ሙዚቃ መጫወት

- ሌሎች ተማሪዎች ሲዘምሩ ወይም ተነጻጻሪ ክፍሎችን ሲጫወቱ በቀላል የከር ኣጃቢ መጫወት።
- በቡድኖች ውስጥ ሆኖ መዘመር፣ ተምቡሮችን በመደባለቅ እና ዳይናሚክ ደረጃዎችን በማጋጠም።

### ለሙዚቃ ምላሽ መስጠት

- የተወሰኑ መሳርያዎችን በማየትና በማዳመጥ መለየት።
- ምርጥ ስራዎች ደረጃውን ከጠበቀ የሙዚቃ ስነፅሁፍ እንዴት ከልዩ ታሪካዊ ክውነቶች ጋር እንደሚዛመዱ ማዳመጥና መግለፅ።

## የአካል ማጠንከርያ ትምህርት

### ጤና-ኣራማጅ ኣካላዊ ብቃትና እንቅስቃሴ

- በልብ ትርታ ግብ ውስጥ ማስላት እና እንቅስቃሴዎችን መስራት።
- ደረጃውን የጠበቀ የአካል ብቃት ፈተናን በመጠቀም፣ ስርዓት ባለዉ አቀራረብ አማካኝነት የራስ የልብና የመተንፈሻ አካላዊ ብቃትን መገምገም።
- ግላዊ የጡንቻ ሃይል፣ የጡንቻ ጥንካሬ፣ እና የመተጣጠፍ ችሎታን ማገናዘብና ማወዳደር።

### የእንቅስቃሴ ክሂሎቶች እና ፅንሰሃሳቦች

- በመያዝ፣ መግፋት፣ እና መወርወር ላይ የሚያስፈልጉ ክሂሎቶችን ማጣራት።
- በእጅ ወይም በእግር እያነጠርክ/ሽ ኳስ የመቆጣጠር ችሎታ አሳይ።

## የጤና ትምህርት

### የኣእምሮና የስሜት ጤንነት (MH)

- ውጤታማ የመግባባት ችሎታዎችን መገንዘብና ተግባር ላይ ማዋል።
- ለተለያዩ ሁኔታዎች ስሜቶችንና ምላሾችን ማገናዘብ።

### ኣልኮል፣ ትምባሆ እና ሌሎች እፆች Alcohol, Tobacco, and Other Drugs (ATOD)

- ሃኪም ለሚያዛቸው መድሃኒቶችና የOTC እፆች ሰላማዊ ልምዶችን መለየት።
- ማሪዋናን ኣእምሮ-የሚያዛባ/psychoactive ህገ ወጥ እፅ መሆኑን መለየት።
- ትምባሆ/ሲጋራ፣ አልኮል፣ እና ማራዋና (አደንዛዥ እፅ) የመጠቀምን ግፊት ለመቋቋም ክህሎትን በማዳበር ተጠቀም(ሚ)።